ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

መዝገብ ቁጥር፡217483

ቀን፡-22-06/2014 ዓ.ም

ለ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

<u>አ/አበባ</u>

በይግባኝ ባይ አቶ አሰድ አህመድ እና በመልስ ሰጪ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መካከል ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት 2ኛ ፍትሐብሔር ችሎት የካቲት 22 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ/ውሳኔ 06 ገፅ ከዚህ መሸኛ ጋር የላክን መሆኑን እንገልፃለን።

አሥራት ማሙዬ ችሮታው
የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሬጂስትራር

የመ/ዝ/ቁ. 217483

ቀን ፡- የካቲት 22 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተኸመ ሽፈራው

ነጋዲን ከድር

ሀብታሙ እርቅይሁን

ይግባኝ ባይ ፡- አቶ አህድ አሕመድ ሁሴን ቀረቡ

መልስ ሰጭ ፡- 1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ወኪል ወንጌል አባተ ቀረበ

2. ብልጽግና ፓርቲ አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ።

<u>ፍርድ</u>

ይግባኝ ባይ በኢትዮጵያ በተካሄደው 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ላይ የግል ተወዳዳሪ ሆነው የቀረቡት መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ/ም ከተደረገው ሀገር አቀፍ ምርጫ ሲሆን ለዚህ ፍርድ ቤት ይግባኝ ክርክር ምክንያት ሆኖ የቀረበው በሶማሌ ክልል ላይ በሚገኘው የመዩ ሙሉቄ ምርጫ ክልል የ2ኛ መልስ ሰጭ ዕጩ ተወዳዳሪ የሆኑት ወ/ሮ አያን አብዲ ሹክሪ ባቀረቡት አቤቱታ በድምጽ መስጫው ዕለት መራጮች የፈለጉትን ፓርቲ ወይም ግለሰብ በነፃነት እንዳይመርጡ መከልከላቸውን፣ የምርጫ አስፈጻሚዎች ጫና እንደነበር፣ የድምጽ አሠጣጥ ሥርዓቱ ሕግና መመሪያ የተከተለ እንዳልነበር፣ መሥፈርት የማያሟሉ መራጮች እንዲመርጡ መደረጉን፣ በመራጮች ላይ ዛቻና ማስፈራሪያ ይደርስ ነበር፣ የካቢኔና የሚሊሻ አባላት ዛቻና ማስፈራያ በመጠቀም መራጮች ለአቤቱታ አቅራቢዋ የሰጧቸውን ድምጽ ከድምጽ መስጫ ሳጥን ውስጥ እንዲወጣ በማድረግ ውጤታቸውን በመሰረዝ አድሎና የምርጫ ማጭበርበር ተግባር የተፈጸመባቸው መሆኑን በመግለጽ በምርጫ ክልሉ የተደረገው ምርጫ ውጤት ተሰርዞ ድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ ጠይቀዋል። 1ኛ መልስ ሰጭም ማስረጃ በመስማት ድጋሚ ቆጠራ እንዲደረግና ተጨማሪ የማጣራት ሥራ እንዲሰራ ካዘዘ በኋላ የቀረበውን የኦዲት ውጤት በመመርመር የመዩ ሙሉቄ ምርጫ ክልል የተደረገው ምርጫ ጥሰት የተፈጸመበት ነው በማለት ውጤቱን በመሰረዝ ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ኅዳር 03 ቀን 2014 ዓ/ም ወስኗል። ይግባኝ ባይም ሕዳር 21 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ ምርጫ ቦርድ በሰጠው ውሳኔ ላይ

ያላቸውን ቅሬታ ለ1ኛ መልስ ሰጭ ያቀረቡ ሲሆን 1ኛ መልስ ሰጭ ሕዳር 27 ቀን 2014 ዓ/ም በጻፈው መልስ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155(4) መሠረት ምርጫ ቦርድ የድምጽ አሰጣጥ፣ ቆጠራና ውጤት ጋር በተገናኘ የሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኙን ማቅረብ ያለበት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሚያቀርብ በስተቀር በዚህ ደረጃ ቦርዱ ውሳኔውን የማይቀይር መሆኑን እንገልጻለን በማለቱ ይግባኝ ባይ የይግባኝ ማመልከቻቸውን ለዚህ ፍርድ ቤት አቅርበዋል።

ይግባኝ ባይ ታሕሳስ 04 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ የይግባኝ ማመልከቻ ይግባኝ ባይ በምርጫ ውድድሩ በክልል ምክር ቤት ምርጫ የግል ተወዳዳሪና አሸናፊ ናቸው። ቅሬታ ያልቀረበባቸውን ምርጫ ጣቢያዎች መርምሮ መወሰኑ ባልተጠየቀ ዳኝነት ነው። ይግባኝ ባይ አቤቱታውን በማያውቅበትና መልስ ባልሰጠበት ሁኔታ የተሠጠው ውሳኔ እንዲሻር ወይም ማስረጃና ክርክሩ በሚሰማበት አግባብ ድጋሚ ታይቶ እንዲወሰን ሲሉ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ይሕ ፍርድ ቤትም ይግባኙን መርምሮ የምርጫ ውጤቱ የተሰረዘው ተገቢውን ሥርዓት ተከትሎ ስለመሆን አለመሆኑ እና በውሳኔው መብታቸው የተነካ ሦስተኛ ወገኖች ቅሬታ የሚያቀርቡበት እና ቅሬታው የሚመረመርበት ሥርዓትን ለማጣራት 1ኛ መልስ ሰጭ መልስ እንዲያቀረብ ታዟል። 2ኛ መልስ ሰጭም በይግባኝ ባይ ማመልከቻ በመልስ ሰጭነት ባይቀርብም ለውሳኔ አሠጣጡ አስፈላጊ ተከራካሪ መሆኑ የታመነበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 40(2) መሠረት በመልስ ሰጭነት መልስ እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ አዟል።

1ኛ መልስ ሰጭ ጥር 20 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ መልስ ቅሬታ በቀረበበት ምርጫ ክልል አቤቱታ አቅራቢዋ ያቀረቡትን ማስረጃ እንዲሁም ለትክክለኛ ፍትሕ አሠጣጥ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች መሠረት ተደርጎና ተጣርቶ በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ የተወሰነ ነው። አቤቱታው የተመረመረው የምርጫ ሂደት ቅሬታዎች የሚቀርቡበትን ሥርዓትና የምርጫ ልዩ ባሕሪን መሠረት ተደርጎ ነው። በምርጫው ሂደት ተሳታፊ የነበረና ይፋዊ ባልሆነ የምርጫ ውጤት መግለጫዎች ላይ አሸናፊ ነው በሚል የተመለከተን ፓርቲ ወይም የግል ዕጩን መጥራትና በክርክሩ የመጥራትና የማሳተፍ ኃላፊነት የለብንም። ይግባኝ ባይ በውሳኔው ላይ ይግባኝ ከማለት ባለፈ 1ኛ መልስ ሰጭ በውሳኔው ላይ ማስተካከያ እንዲያደርግ አቤቱታ የሚቀርብበት ሥነ-ሥርዓት የለም። የቀረበው ይግባኝ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ሲል መልሱን አቅርቧል። 2ኛ

መልስ ሰጭ መጥሪያ ደርሶት መልስ ባለማቅረቡ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፏል። ይግባኝ ባይ እና 1ኛ መልስ ሰጭ በይግባኙ ላይ ክርክር አድርገዋል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ፍርድ ቤቱም ለ1ኛ መልስ ሰጭ ውሳኔ መነሻ የሆነውን አቤቱታ ያቀረቡት የብልጽግና ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪ ወ/ሮ አያን አብዲ ሹክሪ አቤቱታ ለማቅረብ መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? በ1ኛ መልስ ሰጭ ውሳኔ መብቱ ተነክቷል ያለ ሦስተኛ ወገን መብቱን የሚያስከብርበት ሥርዓት ምንድን ነው? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን ከግራ ቀኙ ክርክርና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል።

የመጀመሪያውን ጭብጥ እንደመረመርነው በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የሚቻለው በምርጫ ነው። የአንድ አገር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከሚለካባቸው መስፈርቶች ውስጥ ዋነኛው ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ በማካሄድ የሕዝቦችን ሉአላዊ የሥልጣን ባለቤትነት ማረጋገጥ ነው። ሕዝቦች በቀጥታ ወይም በነፃነት በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸው አማካኝነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ መብት ያላቸው ሲሆን ይህንን መብት በተግባር ለማረጋገጥ ደግሞ በየጊዜው የሚከናወንና ሂደቱም ነፃ ሁሉን አቀፍ፣ ትክክለኛ፣ ቀጥተኛ፣ በእኩልነት ላይ የተመሠረተና በሚስጥር የሚከናወን የምርጫ ሥርዓት መገንባት አስፈላጊ ነው። ምርጫ በማንኛውም መልኩ ከማጭበርበር የፀዳና የመራጩ ሕዝብ ድምጽ የሚከበርበት መሆን አለበት። በምርጫ ሂደት በሕግ የመራጭነት መብት የተሰጣቸው መራጮች የወደፊት ተወካዮቻቸውን በሚመርጡበት ጊዜ የመምረጥ መብታቸው ሙሉ በሙሉ የተከበረ መሆን አለበት። ነገር ግን ምርጫ በሚካሄድበት ጊዜ በምርጫ ሂደት እንደማንኛውም ጉዳይ በተለያዩ ምክንያቶች አቤቱታዎችና ቅሬታዎች ይኖራሉ። እነዚህን ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በየደረጃው ተገቢውን ውሣኔ የሚሰጡ አካላት ይኖራሉ። በምርጫ ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች ፍትሃዊ ውሣኔ ካላገኙ የሕዝቡን መብት የሚያሸራርፉ ከመሆናቸው በላይ ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ ናቸው። በመሆኑም በተለያየ ምክንያት ለሚነሱ ቅሬታዎች የገለልተኝነት እና የግልጽነት መርህን መሠረት ባደረገ መልኩ በመምራት በአጭር ጊዜ ውስጥ ፍትሐዊ ዉሳኔ መስጠት ያስፈልጋል። ይህን ማድረግ ምርጫው ዲሞክራሲያዊ፣

ፌ.ዶ/ ል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ

ነፃና ፍትሐዊ እንዲሆን የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ምርጫ ነክ ግጭቶች እንዳይፈጠሩ የማድረግ ዉጤት ይኖረዋል፡፡

የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዘ የሚነሱት የተለያዩ አለመግባባቶች የሚፈቱባቸዉን ሥርዓቶች እንዲሁም ቅሬታዎችን ተቀብለዉ አልባት የሚሰጡ አካላትን ለይቶ ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ የምርጫ ክልል ጽ/ቤት እና ምርጫ ቦርድ ሆነው ተመልክተዋል፡፡ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 78(4) እና 37 ላይ አንድ ላይ ሲነበቡ በሕግ የተደነገገን የዳኝነት ሥርዓትን የሚከተል የዳኝነት ነክ አካላት በሕግ የመዳኘት ሥልጣን ሊሰጣቸው እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡ የእነዚህ አካላት የዳኝነት ሥልጣን በተፈጥሮ የሚገኝ ሳይሆን በግልጽ ሕግ ለመዳኘት ሥልጣን ሲሰጣቸውና የሚሰሩበት የተደነገገ የዳኝነት ሥርዓት ሲኖራቸውና ይህን ተከትለው ሲሰሩ የሚኖራቸው ሥልጣን ነው፡፡ ይህም በዘመናዊው የመንግሥት ሥርዓት መንግሥት ብዙ ጉዳዮች ላይ ሠፊ ሥልጣን ያለው በመሆኑ ለመንግሥት የሕግ አስፈጻሚ አካል የዳኝነት ነክ ሥልጣን አስፈላጊ በመሆኑ፣ የተወሰኑ ጉዳዮች ደግሞ ፍሬ ነገሮችን ለመመልከት ልዩ ዕዉቀት የሚጠይቁ (specialization) በመሆኑ እና ፍርድ ቤቶች ላይ ያለውን የሥራ ጫና ለማቃለል ሥራ ላይ ይውላሉ፡፡

1ኛ መልስ ሰጭ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7 ላይ ዝርዝር ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን ከእነዚህም መካከል ፓርቲዎችን መመዝገብ፣ መከታተልና መቆጣጠር፣ ምርጫ ማካሄድና ማስፈጸም በሕግ የተሰጠው አስተዳደራዊ ሥልጣኑ ሥር የሚወድቁ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አግባብ በድምጽ ቆጠራና ውጤት ላይ ቅሬታ ያላቸው አካላት አቤቱታቸውንና ማስረጃዎችቻውን አቅርበው ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጉዳዩን መርምሮ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች የዳኝነት ነክ አካል ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የዳኝነት ነክ አካል በሕግ በግልጽ የተለዩ ውስን ጉዳዮችን የሚመለከት ዳኝነት ሰጭ አካል እንደመሆኑ መጠን መደበኛው ፍርድ ቤት የሚመራበት ሥርዓትን መከተል ሳይገባው በሚወጣለት ልዩ ሥነ-ሥርዓት ተከትሎ ውሳኔ

ሊሰጥ ይችላል። ነገር ግን ማንኛውም የዳኝነት አካል ሊከተለው የሚገባ የዳበረ የዳኝነት አሰጣጥ ዝቅተኛ መስፈርቶች አሉ። ዋና ዋናዎቹም የቀረበለትን ጉዳይ ለመመልከት ሥልጣን ያለው መሆኑ፣ ጉዳዩን ያቀረበው ሠው አቤቱታውን ለማቅረብ መብት ያለው መሆኑ (standing right)፣ መብቱ የበሰለ ስለመሆኑ (ripeness)፣ የግራ-ቀኙን ወገን የመደመጥ መብት (basic due process) ያከበረ መሆንና ውሳኔው የተመሠረተው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ መሆን ናቸው።

በተያዘው ጉዳይ በኢትዮጵያ መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ/ም በተካሄደው 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ላይ ለዚህ ፍርድ ቤት ይግባኝ ክርክር ምክንያት ሆኖ የቀረበው በሶማሌ ክልል ላይ በሚገኘው የመዩ ሙሉቄ ምርጫ ክልል የብልጽግና ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪ የሆኑት ወ/ሮ አያን አብዲ ሹክሪ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት 1ኛ መልስ ሰጭም ማስረጃ በመስማት ድጋሚ ቆጠራ እንዲደረግና ተጨማሪ የማጣራት ሥራ እንዲሰራ ካዘዘ በኋላ የቀረበውን የኦዲት ውጤት በመመርመር የመዩ ሙሉቄ ምርጫ ክልል የተደረገው ምርጫ ጥሰት የተፈጸመበት ነው በማለት ውጤቱን በመሰረዝ ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ኅዳር 03 ቀን 2014 ዓ/ም ወስኗል። 1ኛ መልስ ሰጭ ጥሰት መኖር አለመኖሩን በባለሙያ ውጤት እንዲቀርብ ማድረጉ በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 151(10) መሠረት አቤቱታዎች ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚያግዙ የፍሬ ነገር፣ የማስረጃና የሕግ ጉዳዮችን አጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርቡ ባለሙያዎችን በመመልመል ቅሬታዎችን ማጣራት እንደሚችል በተመለከተው አግባብ የፈጸመ መሆኑን ከሚያሳይ በስተቀር ጉዳዩን የወሰነው የብልጽግና ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪ የሆኑት ወ/ሮ አያን አብዲ ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት መሆኑን አያስቀረውም።

በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155(1) መሠረት በድምጽ ቆጠራ ሂደትና በውጤቱ ላይ ለምርጫ ቦርድ አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት፣ የግል ዕጩ ወይም ወኪል ብቻ ስለመሆናቸው ተመልክቷል። ይሕም ለፍርድ ቤቶች አቤቱታ ማቅረብ የሚችለው መብት ያለው ሰው ነው ተብሎ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33 ከተመለከተው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው። 1ኛ መልስ ሰጭ በዳኝነት ነክ ሥልጣኑ አቤቱታዎችን ሲቀበልና ሲመረምር በምርጫ ሕጉ

ፌደራል ጠቅላይ ... ፍ/ቤ
ትክክለኛ ግልባጭ

የተመለከቱ የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች የማክበርና የመፈጸም ኃላፊነት አለበት። ለዚህ ይግባኝ መነሻ የሆነው ውሳኔ የተሰጠው ወ/ሮ አያን አብዲ ሹክሪ ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት በመሆኑ ግለሰቧ አቤቱታ ለማቅረብ ችሎታ ያላቸው መሆን አለመሆኑን መመርመሩ ተገቢ ነው። አቤቱታ አቅራቢዋ የብልጽግና ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪ ሆነው በምርጫ ክልሉ ለክልል ምክር ቤት የተወዳደሩ ሲሆን አቤቱታው ያቀረቡት ፓርቲያቸውን ወክለው አይደለም። በሕጉ አቤቱታ ለማቅረብ መብት የሠጠው ለፖለቲካ ድርጅቶች፣ ለግል ዕጩ ወይም ለሕጋዊ ወኪል በመሆኑ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት የፓርቲው ወኪል ሳይሆኑ በግላቸው በምርጫ ውጤቱ ላይ አቤቱታ የማቅረብ መብት የላቸውም። ስለሆነም 1ኛ መልስ ሰጭ አቤቱታ አቅራቢ ወ/ሮ አያን አብዲ ሹክሪ በምርጫ ውጤት ላይ አቤቱታ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት አቤቱታውን ውድቅ ማድረግ ሲገባው አቤቱታውን ተቀብሎ በሶማሌ ክልል ላይ በሚገኘው የመዩ ሙለቁ ምርጫ ክልል ውጤት በመሰረዝ ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ውሳኔ መስጠቱ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል። በመጀመሪያው ጭብጥ መሠረት ጉዳዩ እልባት ስላገኘ በሁለተኛ ጭብጥ የተመለከተውን መመርመር አላስፈለገም። ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

## ውሳኔ

1. 1ኛ መልስ ሰጭ ሕዳር 03 ቀን 2014 ዓ/ም በሶማሌ ክልል ላይ በሚገኘው የመዩ ሙለቁ ምርጫ ክልል ውጤት በመሰረዝ ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ የሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል።
2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ-ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለተከራካሪዎች እንዲሰጥ አዘናል። 1ኛ መልስ ሰጭ በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል። ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም/ቁ.